# ቀጥታ አቅርቦት እንዲሁም የካፒታል ግንባታ ሲከናወን የተከፈለን የተጨማሪ እሴት ስለማቀናነስ የወጣ መመሪያ

*የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን*

*ነሐሴ 2001 ዓ.ም.*

*አዲስ አበባ*

# ቅይጥ አቅርቦት እንዲሁም የካፒታል ግንባታ ሲከናወን የተከፈለን የተጨማሪ እሴት ታክስ ስለማቀናነስ የወጣ መመሪያ ቁጥር 20/2001

የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢዎች በአዋጁ አንቀጽ 21(2) መሠረት ወደ አገር ባስገቧቸውና በአገር ውስጥ በገዟቸው ዕቃዎች ላይ የከፈሉት የተጨማሪ እሴት ታክስ ሙሉ በሙሉ ተቀናሽ መደረግ ስለሚገባው፣

ከታክስ ማቀናነስ ወይንም ማካካስ ጋር በተያያዘ በከፊል ከታክስ ነፃ እንዲሁም ታክስ ለሚከፈልበት አቅርቦት የዋለ ጥሬ ዕቃ ላይ የተከፈለ ታክስ የሚካካስበትን ስሌት ማውጣት አስፈላጊ በመሆኑ፣

አንድ የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ የካፒታል ማስፋፋት ስራዎች በሚያከናውንበት ጊዜ በግንባታ ሂደት የተከፈለ የግብዓት ታክስ እንዴትና መቼ መቀናነስ እንዳለበት መወሰን በማስፈለጉ፣

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በሚኒስትሮች ምክር ቤት የገቢ ግብር ደንብ ቁጥር 78/1995 አንቀጽ 27 እና በተጨማሪ እሴት ታክስ ደንብ ቁጥር 79/1995 አንቀጽ 39 በተሰጠው ሥልጣን መሰረት ይህንን የአፈፃፀም መመሪያ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ መመሪያ "ቅይጥ አቅርቦት እንዲሁም የካፒታል ግንባታ ሲከናወን የተከፈለን የተጨማሪ እሴት ታክስ ስለማቀናነስ የወጣ መመሪያ ቁጥር 20/2001" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   በዚህ መመሪያ ውስጥ:-

   1) "ታክስ" ማለት የተጨማሪ እሴት ታክስ ነው፡፡
   2) "አዋጅ" ማለት የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/1994 ነው፡፡
   3) "ሰው" ማለት የተፈጥሮና የሕግ ሰው ነው፡፡
   4) "ባለሥልጣን" ማለት የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ነው፡፡

3. <u>የታክስ አቀናነስ</u>

1. በአዋጁ አንቀጽ 21(2) መሠረት ወደ አገር በገቡ እና በአገር ውስጥ በተገዙ ዕቃዎች የታክስ ተቀናሽ ወይም ማካካስ ተፈፃሚ የሚሆነው በቀጥታ ከሥራው ወይም ከአቅርቦቱ ጋር ግንኙነት ባለው ግብዓት ላይ ብቻ ነው::
2. ከታክስ ነፃ ለሆኑ ግብይቶች በዋሉ ወደ አገር ውስጥ በገቡ ወይም ከአገር ውስጥ በተገዙ ዕቃዎች እና አገልግሎቶች ላይ የተከፈለ ታክስ ተቀናሽ አይደረግም::
3. ለአዋጁ አንቀጽ 21 ንዑስ አንቀጽ (2) (ሐ) አፈፃፀም በከፊል ታክስ ለሚከፈልበትና በከፊል ከታክሱ ነፃ ለሆኑ ግብይቶች በዋሉ ወደ አገር በገቡና ከአገር ውስጥ በተገዙ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ላይ የተከፈለን ታክስ የተመዘገበው ሰው ከዚህ በታች በተመለከተው ቀመር መሰረት አስልቶ ማቅረብ አለበት::

$$ተ = ሀ \times ለ/ሐ$$

ለዚህ ስሌት አፈፃፀም፡-

ተ= ታክስ/ክሬዲት ሊደረግ የሚገባ የተከፈለ ታክስ፣

ሀ= በከፊል ታክስ በሚከፈልበት በከፊል ደግሞ ከታክሱ ነፃ በሆነ ግዢ ላይ የተከፈለ ተጨማሪ እሴት ታክስ፣

ለ= የተመዘገበ ሰው በሂሳብ ዘመኑ ውስጥ ያከናወነው ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ዋጋ፣

ሐ= የተመዘገበው ሰው በሂሳብ ዘመኑ ውስጥ ያከናወነው ጠቅላላ ግብይት፣ ተደርገው ተወስደዋል::

4. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 3 (ለ/ሐ) መሠረት የሚገኘው ውጤት ከ0.90 በላይ ከሆነ የተመዘገበው ሰው በአዋጁ አንቀጽ 21 ንዑስ አንቀጽ (2) “ሐ” በተመለከተው መሠረት በአገር ውስጥ በገዛቸው ወይም ከውጭ አገር ባስገባቸው ዕቃዎች ላይ የከፈለው ታክስ ሙሉ በሙሉ ተቀናሽ ይደረጋል::

## 4. ተመላሽ ታክስን በሌላ ሁኔታ ስለማስላት

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 2(3) በተመለከተው መሠረት ማስላት ካልተቻለና የተመዘገበው ሰው ታክስ የሚከፈልበት እና ከታክሱ ነፃ የሆነ ግብይት የሚያካሂድ ከሆነ የታክሱ ባለሥልጣን በሂሳብ ዘመኑ ውስጥ ተቀናሽ የሚደረገውን ታክስ ተገቢ መስሎ በታየው ሌላ ስሌት እንዲከናወን ሊያደርግ ይችላል፡፡

## 5. ከካፒታል ማስፋፋት ጋር ተያይዞ ስለሚደረግ የታክስ ተቀናሽ፣

1. አንድ ለተጨማሪ እሴት ታክስ የተመዘገበ ሰው የንግድ ሥራውን በማስፋፋት ሂደት በመገንባት ላይ ባሉ ህንፃዎች ወይንም ሌሎች ካፒታሎች ላይ የተከፈለን የተጨማሪ እሴት ታክስ፤ ከሌላ ታክስ ከሚከፈልበት ዘርፍ ከተሰበሰበ ታክስ ላይ እንዲያቀናንስ አይፈቀድለትም፡፡
2. በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 4 (1) የተገለፀው ቢኖርም በመገንባት ላይ ያለው ህንፃ ወይንም ሌላ ካፒታል ተጠናቆ ታክስ ለሚከፈልበት የንግድ ተግባር መዋሉ ሲረጋገጥ፣ ወይም ታክስ የሚከፈልበትን ተግባር ለማጠናከር ሲውል በግብዓቱ ላይ የተከፈለውን ታክስ ስራ ሲጀምርና ገቢ ሲያመነጭ ከሚሰበሰበው ታክስ ላይ ማቀናነስ ይቻላል፡፡
3. ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) አፈፃፀም የግብዓት ታክሱ የማስታወቂያ ጊዜ ካፒታሉ ታክስ የሚከፈልበትን ገቢ ማመንጨት ከጀመረበት ወር ጀምሮ ይሆናል፡፡
4. ለሕንፃው ግንባታ ለሥራ ተቋራጭ የተከፈለው የግብዓት ታክስ ተመላሽ የሚሆነው ተቋራጩ ሕጋዊ ፍቃድ ያለው ሲሆንና ተቋራጩ በሚያቀርበው የግብዓት ዋጋ ዝርዝር(Bill of quantity) መሠረት በተከፈለና በተረጋገጠ ታክስ መጠን ነው፡፡
5. የተመዘገበ ሰው የተከፈለ ታክስ ሳይቀነስለት የካፒታሉ አካል ሆኖ እንዲታሰብለት ከፈለገ ዓመታዊ የአገልግሎት ዋጋውን በማስላት በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀጽ 23 መሠረት በንግድ ሥራ ሀብቶች የእርጅና ቅናሽ ሥርዓት ማቀናነስ ይችላል፡፡

6. **የተሻሩ መመሪያዎች**

ከዚህ በፊት የነበሩ መመሪያዎች በዚህ መመሪያ ተተክተዋል፡፡

7. **መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ መመሪያ በባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ተፈርሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ------------- ቀን 2001 ዓ.ም.

መላኩ ፈንታ
የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
ዋና ዳይሬክተር